# WELCOME ABOARD



The year 2011 will soon come to an end and nothing gives me greater pleasure than to share with our dear customers the new and exciting developments enhancing our products and services all across the system.

Our fleet renewal project has successfully celebrated the arrivals of 11 brand new aircraft during the year including the five ultra long-range Boeing 777-200LRs fitted with angled lay-flat bed for the Cloud Nine class making the long distance travel of our customers more comfortable and enjoyable. Furthermore, the seats are fitted with the state-of-the-art in-flight entertainment system offering the choice of over 80 channels. The deployment of these aircraft has enabled us to operate daily non-stop from Washington to Addis Ababa; and, between Addis Ababa and Beijing, thereby reducing the flying time on both legs by over three hours in each direction. Our loyal customers will also be delighted to learn that we have retrofitted our existing aircraft with new seats both in Economy and Business class.

However, the renewal project will not be quite complete until the delivery and arrival of the long awaited member of our young fleet. The breaking news is that Ethiopian will take delivery of its first 787 Dreamliner during the first quarter of 2012. With this ultra modern aircraft, the first of its kind in Africa, we are convinced that our customers will have the ultimate travel experience.

As one of the milestones of this year's achievements, Ethiopian will, at the end of this year, be joining the largest airline alliance in the world, the Star Alliance. This new partnership will bring enormous choices and flexibility to our customers such as daily departures to over 1,000 destinations and free use of lounges at a number of airports around the globe.

In our continued effort to take our customer services to the next level and provide adequate support for all the new developments, our Aviation Academy has signed a three years customer services culture change training contract with a United States based, Services Quality Institute, to train 2,000 of our front line customer service staff. The first round of this training programme is already in progress.

As part of our strategic network expansion plan we will soon add exciting new destinations like Toronto in Canada and Victoria in Seychelles to our route network.

Last but not least is our pledge to our customers. As part of our corporate social responsibility, we have an open pledge to our customers to plant a tree every time they fly with us. In the last two years alone, we have planted over 7.5 million trees under this programme and it is bound to continue. We therefore request you to support this noble initiative by flying with us.

With all these exciting developments and more to come, Ethiopian would like to once again assure you of its unreserved efforts to make your travel experience an enjoyable and a memorable one.

On behalf of the management team and the entire staff, I would like to take this opportunity to thank you for your continued support and patronage.

Thank you for flying Ethiopian.

Enjoy your flight!

Tewolde GebreMariam
Chief Executive Officer, Ethiopian Airlines

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመብረር እንኳን ደህና መጡ::

በቅርቡ በመጠናቀቅ ላይ በሚገኘው የአውሮፓዊያኑ 2011 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ያስመዘገበውን ታላቅ እድገት ለክቡራን መንገደኞቻችን ለማካፈል በመቻሌ የተሰማኝን ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ::

የአውሮፕላኖቻችንን አይነት እና ብዛት ለማሻሻል ባደረግነው እንቅስቃሴ አስራ አንድ አዳዲስ አውሮፕላኖችን በዚህ ዓመት ማስመጣት ችለናል። ከነዚህም ውስጥ አምስቱ ለረጅም ርቀት በረራ የሚያገለግሉ የቦይንግ 777-200LR አውሮፕላኖች ናቸዉ። እነዚህ አውሮፕላኖች በክላውድ ናይን ክፍሎቻቸው ውስጥ ለመተኛት የሚያስችሉ መቀመጫዎች ያሏቸው ከመሆኑም ባሻገር ከ80 በላይ የመዝናኛ ቻናሎችን ያካተቱ የመዝናኛ መሳሪያዎች የተገጠመላቸው ናቸው:: እነዚህን ዘመናዊ አውሮፕላኖች በማስመጣታችን ቀድሞ የነበረውን የበረራ ግዜ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ከ3 ሰአት በላይ በመቀነስ ከዋሽንግተን - አዲስ አበባ እንዲሁም ከአዲስ አበባ ቤጂንግና ከቤጂንግ አዲስ አበባ የቀጥታ በረራ እንድናደርግ አስችሎናል። ሌላው ለደንበኞቻችን ያለን መልካም ዜና፣ በማገልገል ላይ ያሉ አውሮፕላኖቻችንን መቀመጫዎች በአዲስ መልክ መቀየራችን ነው:: ይህም መንገደኞቻችንን በምቾት እንዲጓዙ ያስችላል::

ይህ ሁሉ የአገልግሎት ጥራት ማሻሻያ እርምጃችን የላቀና ምሉዕ የሚሆነው ለረዥም ጊዜ በጉጉት ስንጠብቀው የነበረውና እጅግ ዘመናዊ የሆነውን ቦይንግ 787 አውሮፕላን ስንረከብ ነው። በቅርቡ በወጣው ዜና መሰረት የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአውሮፓውያን የዘመን ቀመር በ2012 በመጀመሪያዎቹ ወራት የመጀመሪያውን ቦይንግ 787 አውሮፕላን ይረከባል:: በዚህ እጅግ ዘመናዊና በአፍሪካ የመጀመሪያ በሆነው አውሮፕላን ደንበኞቻችን የሚያደርጉት በረራ እጅግ የሚያስደስትና ልዩ እንደሚሆን ጥርጥር የለንም::

በዚህ ዓመት ከምናሳካቸው ታላላቅ ግቦች አንዱ የኢትዮጵያ አየር መንገድን የትልቁ የአለም አየር መንገዶች ህብረት "Star Alliance" አባል የማድረግ ነው:: ይህም በያዝነው የአውሮፓውያን ዓመት መጨረሻ ላይ እውን ይሆናል:: አዲሱ ህብረት ከሚፈጥራቸው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችና የበረራ አማራጮች መካከል ከአንድ ሺህ በላይ ወደሚሆኑ የበረራ መዳረሻዎች በየቀኑ መብረር እንዲሁም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ በርካታ አውሮፕላን ማረፊያዎች ውስጥ የነጻ የማረፊያ አገልግሎት ማግኘትን ያካትታል::

የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጣችንን ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስና አዲስ እየተመዘገቡ ያሉ እድገቶችን ለመደገፍ ያስችል ዘንድ፣ የአቪየሽን ማሰልጠኛ ተቋማችን አሜሪካን ሀገር ከሚገኘው "Service Quality Institute" ከተሰኘ ተቋም ጋር የሶስት ዓመት የስልጠና ስምምነት ተፈራርሟል። በዚህም መሰረት ለሁለት ሺህ የደንበኞች አገልግሎት ሠራተኞች ስልጠና ይሰጣል። በአሁኑ ወቅት የስልጠናው የመጀመሪያ ዙር በመገባደድ ላይ ይገኛል።

አለም አቀፍ የበረራ መዳረሻዎቻችንን ለማስፋፋት ባወጣነው እቅድ መሰረት በቅርቡ ወደ ካናዳ ቶሮንቶ እና የሲሸልስ ዋና ከተማ ወደ ሆነችው ቪክቶሪያ የበረራ አገልግሎት መስጠት እንጀምራለን።

በመጨረሻም የማህበራዊ ኀላፊነታችንን ለመወጣት በምናጓጉዘው በእያንዳንዱ መንገደኛ ቁጥር ዛፍ ለመትከል ቃል ገብተናል። ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥም ከ7.5 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን የተከልን ሲሆን ይህም በመጪዎቹ ዓመታት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። ይህን ታላቅ ዓላማ ለመደገፍ ከኛ ጋር እንድትበሩ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

እስካሁን የታዩ አመርቂ እድገቶችንና ወደፊትም የሚመዘገቡትን ውጤቶች በአንድነት በመቀመር የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራዎን አስደሳችና ሁሌም የሚታወስ ለማድረግ እንደምንተጋ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

በኢትዮጵያ አየር መንገድ አመራር አባላትና በመላው ሰራተኞች ስም ከኛ ጋር ስለበረራችሁና ለቀጣይ ድጋፋችሁ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ።

መልካም በረራ!